washington healthplanfinder

click. compare. covered.

የዋናዋና የጤና መድህን ዝርዝሮች

# የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመርያዎች



የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመርያዎች

# ተቀናሽ

## ተቀናሽ ምንድን ነው?

ተቀናሽ ማለት የጤና እቅድዎ ወጪ መጋራት ከመጀመሩ በፊት ለእንክብካቤዎ መክፈል ያለብዎት መጠን ነው። የተቀናሽ መጠን በእያንዳንዱ ዓመት መጀመርያ ላይ ይጀምራል።

## በምን መልኩ ይሰራል

ማርቆስ (Marcus) $2,000 ተቀናሽ ኣለው። በሆስፒታል ውስጥ $10,000 ከፍሏል። ማርቆስ የጤና ሽፋኑ ለነዚህ ወጪዎች መክፈል ከመጀመሩ በፊት ተቀናሽ መክፈል ይኖርበታል።
*(ተቀናሽ እና ሌሎች ወጪዎች እንደየ ጤና እቅዱ ይለያያል።)*



የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመርያዎች

# እቅድ ፎርሙላሪ

## እቅድ ፎርሙላሪ ምንድን ነው?

እቅድ ፎርሙላሪ ማለት የጤና እቅድዎ የሚሸፍናቸው የመድሀኒት ዝርዝሮች ናቸው። የጤና እቅድዎ ለነዚህ መድሀኒቶች በሙሉ ወይ በከፊል ይከፍላል።

## በምን መልኩ ይሰራል

ጆርጅ (George) አዲስ መድሀኒት ሊገዛ ወደ ፋርማሲ ይሄዳል። ጆርጅ የፋርማሲ ዝርዝር እቅድ ፎርሙላሪ ይዟል። የጤና እቅዱ ለዚህ መድሀኒት ይከፍላል። ጆርጅ $20 ወጪ መጋራት ይከፍላል እቅዱ ደግሞ የቀረውን ክፍያ ይከፍላል።
*(ወጪ መጋራት ክፍያ እንደየ ጤና እቅዱ ይለያያል።)*



**$20**

ለእያንዳንዱ ለታዘዘው መድሀኒት

የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመርያዎች

# የመጀመርያ የጤና እርዳታ ሰጪ

## የመጀመሪያ የጤና እርዳታ ሰጪ ምንድነው?

የመጀመርያ የጤና እርዳታ ሰጪ የጤና እቅድዎ አካል በመሆኑ የሚያክሞት ዋና ሀኪም ወይ ነርስ ነው። የመጀመርያ ደረጃ እርዳታ ሰጪ የጤና እንክብካቤውን የሚመራ ነው። የእርስዎን ጤንነት ለመጠበቅ ከስፔሻሊስት ጋር ሊሰሩ ይችላሉ።

## በምን መልኩ ይሰራል

ከዚህ ቀደም ሮጀር የህመም ስሜት ስለተሰማው ወደ ድንገተኛ ክፍል ሄደ። አሁን፡ የመጀመርያ የጤና እርዳታ ሰጪ መምረጥ የሚያስችለው የጤና እቀድ አለው፡ ፡ ሲያመው ወደ መጀመርያ የጤና እርዳታ ሰጪው ጋር በመሄድ መታከም ይችላል፡ ፡ ሮጀር በሽፔሻሊስት ህክምና የሚያስፈልገው ከሆነ የመጀመርያ የጤና እርዳታ ከስፔሻሊስት ጋር ያገናኘዋል።



ለምርመራ፣ አስቸኳይ ላልሆነ እንክብካቤ እና በቨርቹዋል ለሆነ እንክብካቤ የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ አቅራቢዎን ይጎብኙ።

የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመሪያዎች

# ፕሪምየም
# የግብር ክረዲት

# ፕሪምየም የግብር ክረዲት

## ፕሪምየም ግብር ክረዲት ምንድን ነው?

የግብር ክረዲት በወር ለጤና እቅድ ከሚከፍሉት መጠን በታች ነው። የሚያገኙት የግብር ክረዲት ገቢዎን መሰረት ያደረገ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት **wahealthplanfinder.org** ይጎብኙ ወይ ወደ **1-855-923-4633** ይደውሉ።

## በምን መልኩ ይሰራል

ማርኬላ (Marcela) ያላገባችና የጤና እቅድ የሌላት አዋቂ ናት። ዓመታዊ ገቢዋ $25,000 ነው። የገቢ ደረጃዋ ምክንያት የግብር ክረዲት ታገኛለች። ማርኬላ ወርሀዊ ክፍያዋ እንዲቀንስላት የግብር ክሬዲቷን መጠቀም ትችላለች።
*(ትክክለኛው ቁጥር ሊለያይ ይችላል።)*



የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመርያዎች

# የጋራ -መድህን

## የጋራ መድንህን ምንድን ነው?

የጋራ መድንህን የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ለሚሸፍነው የእርስዎ የሚከፍሉት ድርሻ ነው። የጋራ መድንህን የሚከፍሉት የጤና እቅድ ተቀናሽ ከከፈሉ በኋላ ነው። የጋራ መድንህን ከጤና እቅድዎ ጋር ለጤና እንክብካቤዎ ወጪ የሚጋሩበት አንዱ መንገድ ነው።

## በምን መልኩ ይሰራል

ጄምስ (James) ተቀናሽ ከፍሏል። ወደ ህክምና ሲሄድ $500 ይከፍላል። ጄምስ ከዚህ ወጪ 20% ወይ $100 ይከፍላል። የጤና እቅዱ የቀረውን የክፍያ መጠን ይከፍላል። *(የጋራ መድህን ክፍያ እንደየ ጤና እቅዱ ይለያያል።)*



**20%** የጋራ መድህን

x **$500** አጠቃላይ ሒሳብ

---

**$100** ጄምስ የሚከፍለው

የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመርያዎች

# የአረቦን ክፍያ፡-

## ፕሪምየም ምንድን ነው?

ፕሪምየም ማለት ለጤና እቅድዎ በየወሩ የሚከፍሉት መጠን ነው። ምንም የጤና መድን ክብካቤ አገልግሎቶችን የማይቀበሉ ያሉ እንኳ ቢሆን የእርስዎን አርቦን የመክፈል ግዴታ አለብዎት። ስለ ማንኛውም ክፍያ የሚኖሩት ጥያቄ ለመድህን አቅራዎ ያግኙ።

## በምን መልኩ ይሰራል

ጄን (Jean) በየወሩ ልክ እንደ ስልክ ሒሳብዋ ለጤና እቅድ ፕሪምየም ትከፍላለች፡ ፡ ጄን ክፍያዋ በግዜው እንዲደርስ ክፍያዋን አስቀድማ ትከፍላለች ወይ ኦንላይን ትከፍላለች።




አስቀድመው በመክፈል ክፍያው ጥቅም ላይ እንዲውል ግዜ ይስጡት።

የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመርያዎች

# ከኪስ የሚከፈል ክፍያ

## ከኪስ የሚከፈል ክፍያ ምንድን ነው?

ከኪስ የሚከፈል ክፍያ ማለት እርስዎ ለጤና እንክብካቤዎ የሚከፍሉት ክፍያ ነው። ተቀናሽ፣ የጋራ መድህንና የጋራ ክፍያ ሊያካትት ይችላል። በጤና እቅድዎ ሽፋን ያላገኘ ማንኛም ክፍያ ከኪስ የሚከፈል ነው።

## በምን መልኩ ይሰራል

ሺርሊ (Shirley) ሁለት ልጆች አልዋት። እሷና ልጆቿ ወደ መደበኛ የሀኪም ቀጠሮ ሲሄዱ $20 ይከፍላሉ። ቤተሰቡ በዓመት ውስጥ 15 መደበኛ የሀኪም ቀጠሮ አላቸው፡ ፡ ሺርሊ ከኪስዋ የምትከፍለው ክፍያ መጠን $300 ይሆናል።
*(ቁጥሮቹ ግምታዊ ነው። ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ወደ መድህኖ ይደውሉ።)*



**$20** በእያንዳንዱ አገልግሎት

x **15** ግዜ

---

**$300** በዓመት

የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመርያዎች

# ኔትዎርክ

## ኔትዎርክ ምንድን ነው?

ኔትዎርክ ማለት የጤና እቅድዎ የሚሸፍነው የኔትዎርክ ዝርዝር ነው። የኔትዎርክ ውስጥ አቅራቢ በጤና እቅድዎ ተቀባይነት ያገኘ አቅራቢ ነው። ከኔትዎርክ ውጪ ያሉት አቅራቢዎች በጤና እቅድዎ ተቀባይነት የለቻውም። ከኔትዎርክ ውጪ በሆኑ አቅራቢዎች አገልግሎት ሲያገኙ ተጨማሪ ክፍያ ይከፍላሉ።

## በምን መልኩ ይሰራል

ላውራ (Laura) የአእምሮ ጤና ሀኪም እንዲያክማት ትሻለች። በእርስዎ አቅራብያ ያለውን አገኘች። ቀጠሮ ከመያዝዎ በፊት አቅራቢው በጤና እቅድ ኔትዎርኮ ውስጥ መሆኑን ያረጋግጡ። ላውራ ከኔትዎርክ ውጪ የሆነ አማካሪ ከመረጠች ብዙ ወጪ ያስወጣታል።




ቀጠሮ ከመያዘ በፊት አቅራቢዎ በኔትዎርክ ውስጥ መሆናቸውን ይጠይቁ።

የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመርያዎች

# የጋራ ክፍያ

## የጋራ ክፍያ ምንድን ነው?

የጋራ ክፍያ ማለት ሽፋን ላገኙበት የጤና እንክብካቤ የሚከፍሉት የክፍያ መጠን ነው። እንደ መደበኛ ሕክምና ወይ መድሀኒት ግዢ የጋራ ክፍያ አላቸው። የጋራ ክፍያ የሚከፍሉት አገልግሎቱን ሲያገኙ ነው፥

## በምን መልኩ ይሰራል

ቶማስ (Thomas) የደም ግፊት አለው። በየሶስት ወሩ ወደ መጀመርያ ደረጃ እንክብካቤ አቅራቢው መሄድ አለበት። ለዚህ አገልግሎት ለጤና እቅዱ $20 የጋራ ክፍያ መክፈል አለበት። ቶማስ በሚሄድቤት በእያንዳንዱ ግዜ የጋራ ክፍያ መክፈል አለበት። *(ወጪ መጋራት ክፍያ እንደየ ጤና እቅዱ ይለያያል።)*



**$20**

በእያንዳንዱ አገልግሎት

የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመርያዎች

# የመከላከል አገልግሎት

## የመከላከል አገልግሎት ምንድን ነው?

የመከላከል አገልግሎት እርስዎ ምንም ሳይከፍሉ ወይ በጥቂት ክፍያ በጤና እቅድዎ የሚከፈል ነው። ዓመታዊ ምርመራና የኢንፍሉዌንዛ ክትባት ያካትታል። እነዚህ አገልግሎቶች ሽፋን የሚያገኙት በኔትዎርክ ውስጥ ወደደ ሆነ ኣቅራቢ ሲሄዱ ነው።

## በምን መልኩ ይሰራል

ታይለር (Taylor) ጤናውን ለመጠበቅ ዓመታዊ ምርመራና ኢንፍለወንዛ ክታባት ይከተባል። ታይለር ከመታመም ለሚከላከልለት የጤና እቅድ መክፈሉ ደስ ይለዋል።



የመከላከል አገልግሎት ጤናዎን እንዲጠብቁ ያስችሎታል።

የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመርያዎች

# መሰረታዊ የጤና ጥቅማጥቅሞች

## መሰረታዊ የጤና ጥቅማጥቅሞች ምንድን ናቸው?

መሰረታዊ የጤና ጥቅማጥቅሞች ማለት ሁሉም እቅዶች የሚሸፍኗቸው የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ናቸው። አንዳንዶቹ በነፃ የሚሰጡ ናቸው። አንዳንዶቹ ወጪ መጋራት ወይ የጋራ መድሕን ያላቸው ናቸው።

መሰረታዊ የጤና ጥቅማጥቅሞች የሚያካትቱት፡

- በሀኪም መታከምና ሆስፒታል መተኛት
- ወደ ድንገተኛ ክፍል መግባት
- በእርግዝና ግዜና ከወሊድ በኋላ ክትትል
- የአእምሮ ጤናና የሴስ ህክምና አገልግሎት
- የሚታዘዙ መድሀኒቶች
- ጉዳት ከደረሰቦት ወይ አካል ጉዳት ወይ ቋሚ ህመም ካልዎት እንዲያገምሙ የሚያግዝ አገልግሎትና መሰርያ።
- የላብራቶሪ ምርመራ
- ካውንስሊንግ፣ ምርመራና ክትባት ጨምሮ የመከላከል አገልግሎቶች።
- እንደ ስኳር ወይ አስም የመሳሰሉ ቋሚ ህመም መከታተል።
- የህፃናት ህክምና

## በምን መልኩ ይሰራል

ሁሉም የጤና እቅዶች ተኝቶ መታከምን ማካተትረ አለባቸው። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወደ *Washington Healthplanfinder* ወይ መድሕን ሰጪዎ ይደውሉ። ቁጥራችን **1-855-923-4633**።

**Washington Health Benefit Exchange** የፌደራል ሲቪል መብት ሕግን ያከበረ ነው። በዘር፣ ቀለም፣ ትውልድ ሀገር፣ ዕድሜ፣ አካል ጉዳት ወይ ፆታ መሰረት በማድረግ አድልዎ አንፈፅምም።

የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመሪያዎች

# Cascade Care

## CASCADE CARE ምንድን ነው?

የትኛውንም ተንከባካቢ ቢመርጡም ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ የጤና እቅዶች ናቸው። ከአብዛኞቹ እቅዶች ዝቅተኛ ተቀናሽ ያለው ሲሆን ተቀናሽ ቅድመ ሁነት ከሟሟላቱ በፊት ብዙ አገልግሎቶችን ይሸፍናል።

## CASCADE CARE SAVINGS ቁጠባ ምንድናቸው?

የCascade Care Savings ቁጠባ ፕሮግራማ የጤና እቅድ ፕሮሚየም ወጭዎን ይቀንሳል። ብቁ ከሆኑ፣ ከፍሉን የፕርሚየምዎን መንግስት ይከፍላል።

እነዚህ ነገሮች እውነት ከሆኑ እርስዎም ለCascade Care Savings ቁጠባ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡-

- ገቢዎ ከፈደራል የድህነት ወለል በ250% ያነሰ ነው።
- ለ Washington Apple Health (Medicaid) ወይም Medicare ብቁ ኤደሉም።
- በ Cascade Care የነሃስ ወይም የወርቅ እቅድ ተመዝግበሃል።
- ለታክስ ክሬድቶች ብቁ ከሆኑ፣ ማግኘትት የሚችሉትን መጠን በሙሉ ተቀብለዋል።

## በምን መልኩ ይሰራል

ጄን (Jen) ተቀናሽ ቅድመ ሁነት ከሟሟላቶ በፊት እንክብካቤ ማግኘት ትፈልጋለች። በ *Washington Healthplanfinder* Cascade Care በመምረጥ ጄን በቅድምያ ክፍያ ሳትከፍል መሰረታዊ የጤና ጥቅሞችን ታገኛለች።



የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመርያዎች

# ክፍት ምዝገባ


# ክፍት ምዝገባ

## ክፍት ምዝገባ ምንድን ነው?

ክፍት ምዝገባ ለብቁ የጤና እቅድ መመዝገብ የሚችሉበት ወቅት ነው። በእያንዳንዱ ዓመት ኖቨምበር 1 ይጀምራል። በማንኛውም ሰዓት ለ Washington Apple Health ማመልከት ይችላሉ።

## በምን መልኩ ይሰራል

ጃክሰን (Jackson) ለጤና እቅድ መመዝገብ ይፈልጋል። በ **wahealthplanfinder**.org ወይ **WAPlanfinder** መተግበርያ ላይ ሒሳብ ይከፍታል። ጃክሰን ከኖቨምበር 1 ጀምሮ የሚስማማውን የጤና እቅድ ለማግኘት መግዛትና ማወዳደር ይችላል። ቀነ ገደቡ ከመድረሱ በፊት ይመዘገባል። የጤና እቅዱ በሚቀጥለው ዓመት ጥር 1 ይጀምራል።




ለጤና እቅድ ለመመዝገብ **wahealthplanfinder.org** ይጎብኙ ወይ ከ **WAPlanfinder** መተግበርያ ያውርዱ።

የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመርያዎች

# ልዩ ምዝገባ ግዜ


## ልዩ ምዝገባ ግዜ ምንድን ነው?

አንዳንድ የሂወት ሁነቶች በማንኛውም ሰዓት ለጤና እቅድ እንድትመዘገቡ ያስችላሉ። ይህም ልዩ ምዝገባ ግዜ ተብሎ ይጠራል። ሁነቱ ከተፈጠረ በኋላ ለልዩ ምዝገባ ግዜ ለማመልከት 60 ቀናት አልዎት። (የብቁ የሂወት ሁነት አብነቶችን ይመልከቱ)

የጤና ሽፋን የሚሰጡ የጤና እንክብካቤ ልዩ የምዝገባ ወቅት መስጠት አለባቸው። ይህ ለ30 ቀናት ይቆያል።

## በምን መልኩ ይሰራል

ማያ (Mia) ሚስት ወለደች። ይህ ሁነትም ለልዩ ምዝገባ ግዜ እንድታመለክት ያስችላታል። በ60 ቀናት ውስጥ ወደ *Washington Healthplanfinder* በመግባት ታመለክታለች። አሁን ህፃኑን የሚያካትት አዲስ እቅድ መምረጥ ትችላለች።



ወሊድና ልጅ በማደጎ መውሰድ የጤና እቅዶን መቀየር የሚያስችሉ ሁነቶች ናቸው።

የተጠቃሚዎች ቁልፍ መመርያዎች


# ብቁ የሂወት ሁነት

## ብቁ የሂወት ሁነት ምንድን ነው?

ብቁ የሆነ የሂወት ሁነት ማለት በማንኛውም ሰዓት ለጤና እቅድ ለማመልከት የሚያስችሎት ነው። መኖርያ መቀየር፣ እርግዝና የገቢ ለውጥ የሚሉትን ለውጦች ያካትታል። ሁነቱ ከተፈጠረ በኋላ ለልዩ ምዝገባ ወቅት ለማመልከት 60 ቀናት ኣልዎት። *(የበለጠ መረጃ ለማግኘት የልዩ ምዝገባ ግዜ ይመልከቱ)*

## ብቁ የሆነ የሂወት ሁነት

- ጋብቻ ወይ ወደ ዘቤታዊ ግንኙነት ውስጥ መግባት
- መውለድ
- ልጅ ማሳደግ ወይ ፎስተር ኬር
- የፍርድ ቤት ትእዛዝ (የልጆች ማሰድግያ ጨምሮ)
- በሞት፣ ፍቺ ወይ ሕጋዊ ፍቺ ምክንያት ጥገኛ ማጣጥ ወይ የጥገኝት ሁነት ማጣት
- የገቢ መቀየር
- ሌላ የጤና ሽፋን ማጣት
- ወደ ዋሽንግተን መግባት ወይ ዋሽንግተን ወደ እሚገኙ ወረዳዎች መምጣት
- የዜግነት ሁነት ለውጥ ወይ ሕጋዊ ማንነት ለውጥ
- ከእስር ቤት መውጣት
- የትራይባል ኣባልነት




ሁነቱ ከተፈጠረ በኋላ ለልዩ ምዝገባ ወቅት ለማመልከት 60 ቀናት ኣልዎት።

washington
healthplanfinder
click. compare. covered.

wahealthplanfinder.org
1-855-WAFINDER | 1-855-923-4633